# ***መመሪያ ቁጥር ገባ/12/2003***

## ***ግብር የመክፈል ግዴታቸውን ያልተወጡ ግብር ከፋዮችን ሀብት በመያዝና በመሸጥ የግብር አሰባሰብ የሚከናወንበትን ሥርዓት ለመወሰን የወጣ ማሻሻያ መመሪያ***

1. ***የመመሪያው አስፈላጊነት:***

የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 76/94 አንቀጽ78፣ የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር285/94 አንቀጽ31፣ የተርን ኦቨር ታክስ አዋጅ ቁጥር 83/95 አንቀጽ13 እና የኤክሣይዝ ታክስ አዋጅ ቁጥር 103/96 አንቀጽ10 ግብር ወይም ታክስ እንዲሁም በከተሞች ፋይናንስ ደንብ ቁጥር 37/1998 እና በገቢ አርዕስትና ታሪፍ መወሰኛ ደንብ ቁጥር 69/2001ዓ.ም ግብር ታክስ እና የአገ/ክፍያየመክፈል ግዴታቸውን ያልተወጡ ግብር ከፋዮችን ሃብት በመያዝ ሸጦ ለግብር ወይም ለታክስ ክፍያ እንዲውል ለግብር ሰብሳቢው አካል ሥልጣን የሚሰጡ በመሆኑ::

አዋጆቹና ደንቦችን በተግባር በመተርጐም ሂደት ሊከሰቱ የሚችሉ ችግሮችን ከወዲሁ ለማስወገድና ለመቅረፍ የተዛባ አሠራር እንዳይኖር ለማድረግ አንድ ወጥ የሆነ የአፈፃፀም መመሪያ ማውጣት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ይህ መመሪያ ወጥቷል::

## ክፍል አንድ

## አጠቃላይ ድንጋጌዎች

2. አውጭው ባለስልጣን:

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ገቢዎች ባለሥልጣንን እንደገና ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 168/2002 አንቀጽ 17 ይህንን አዋጅ ለማስፈፀም የሚያስፈልጉትን መመሪያዎች ለማውጣት ስልጣን በተሰጠው መሠረት ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

3. አጭር ርዕስ:

ይህ መመሪያ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ገቢዎች ባለሥልጣን «የግብር/ ታክስና ኪራይ የአገ/ክፍያ ግዴታቸውን ያልተወጡ ግብር/ታክስ ከፋዮችን ሃብት/ ንብረት በመያዝ፣ በመሸጥ ዕዳውን መተካት/በማስመለስ ገቢ ማድረግ የሚያስችል የገቢዎች ባለሥልጣ የወጣ ማሻሻያ መመሪያ ገባ/12/2003 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

4. <u>ትርጓሜ፡</u>

በዚህ መመሪያ ውስጥ ፡.

1. «ግብር ወይም ታክስ" ማለት እንደሁኔታው በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 76/94፣ በተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285/94 በተርን ኦቨር ታክስ አዋጅ ቁጥር 83/95 እና ኤክሣይዝ ታክስ አዋጅ ቁጥር 103/96 መሠረት መከፈል ያለበት ግብር ወይም ታክስ ነው።

2. የአገልግሎት ክፍያ ማለት አንድ ሰው ወይም ድርጅት ዕቃ አገልግሎት ከከተማ አስተዳደሩ /ማ/ቤት በመግዛቱ የዕቃውን የአገልግሎት ዋጋ እንደ አጠቃቀሙ ተሰልቶ እንዲከፍል በህግ የሚጣል የከፍያ ግዴታ ነው።

3. ኪራይ ማለት ግለሰብ /ህጋዊ ሰውነት የተሰጠው አካል የከተማ አስተዳደሩ የማ/ቤቱን ሃብትና ንብረት እንዲጠቀምበት በያዘው ይዞታ ለተጠቀመበት አገልግሎት በተከራዩ እና በከተሞች መካከል በተደረሰ ውል መሠረት የሚከፈል ክፍያ ነው።

4. «**ግብር**/ታክስ ከፋይ" ማለት ግብር ወይም ታክስ እንዲሁም የከተማ አስተዳደር የአገልግሎት መጠቀሚያ ክፍያዎችን የመክፈል ግዴታ የተጣለበት /ያለበት ማናቸውም ሰው ወይም ድርጅት ነው።

5. «የግብር/ታክስ **አስገቢ** ባለስልጣን" ማለት በክልሉ በተለያዩ ደረጃዎች የተቋቋሙ የገቢ ሰብሳቢ አካላት ናቸው።

6. **ዋና ዳይሬክተር** ማለት በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግሥት ገቢዎች ባለሥልጣን የገቢ አሰባሰቡንና ክትትሉን እንዲሁም ማዘጋጃ ቤቶችንና የከተማ አገልግሎት ጽ/ቤቱን በበላይነት የሚመሩ ናቸው።

7. «ሀብት ወይም ንብረት ማለት በገቢ ግብር አዋጅ 76/94 አንቀጽ 78(7) ከመያዝ ነፃ ከተደረጉት በስተቀር የግብር/ታክስ ከፋዩ በሊዝ የያዘውን መሬት ጨምሮ ማናቸውም ቤት ወይም ህንፃ የንግድ ሥራ የሚከናወንበት ድርጅት፣ ልዩልዩ ዕቃዎች፣ በሌላ ሰው ዘንድ ያለው ወይም ከሌላ ሰው የሚያገኘው ወይም የሚከፈለው ገንዘብ፣ ቼኮች፣ የሚተላለፉ ሰነዶች፣ ቦንዶች ወይም ለገንዘብ የተሰጡ ሌሎች ዋስትናዎች፣ በኩባንያ ውስጥ ያለው የአክስዮን ድርሻዎች፣ በጋራ በተያዙ ንብረቶች ያለው ድርሻ ወይም ማናቸውም ሊሸጡ የሚችሉ ሌሎች ገንዘብና ንብረቶች ናቸው።

8. «የገቢ አሰባሰብ ክትትል ሠራተኞች" ማለት የግብር/ታክስ የመክፈል ግዴታቸውን ያልተወጡ ማናቸውንም ሰው ሃብት ወይም ንብረት በማናቸውም መንገድ

እንዲያዝ እንዲከበርና እንዲሸጥ በማድረግ ግብር/ታክስ የማሰባሰብ ተግባር እንዲያከናውኑ የተመደቡ የባለስልጣኑ ሠራተኞች ናቸው፡፡

9. **"የከተማ አስተዳደር ገቢዎች ጽ/ቤት ኃላፊ እና ዞን ወይም ወረዳ ገቢዎች ጽ/ቤት ኃላፊ"** ማለት በገቢ ሰብሳቢው ጽ/ቤት የግብር/ታክስ የአገልግሎት ክፍያ አሰባሰቡንና ክትትሉን በበላይነት የሚመራ የሥራ ኃላፊ ነው፡፡

10. **ንብረት ማስከበር"** ማለት የግብር አስገቢው ባለሥልጣን መ/ቤት የግብር ከፋዩን ሃብት ወይም ንብረት ከመያዙ በፊት ባለበት እንዲቆይና እንዳይንቀሳቀስ የሚወስደው እርምጃ ነው፡፡

11. **"መያዝ"** ማለት በማናቸውም መንገድ መያዝ እንዲሁም የግብር ከፋዩ የሆነ ገንዘብ/ንብረት በእጁ ከሚገኝ ሰው ግብር መሰብሰብን ይጨምራል፡፡

5. *<u>የመመሪያው ተፈፃሚነት ወሰን፡-</u>*

ይህ መመሪያ በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 76/94 በተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285/94 በተርን ኦቨር ታክስ አዋጅ ቁጥር 83/95 እና በኤክሣይዝ ታክስ አዋጅ ቁጥር 103/96 እንዲሁም በከተሞች የገቢ አርዕስትና ታሪፍ መወሰኛ ደንብ ቁጥር 69/2001 በከተሞች የፋይናንስ ደንብ በክልሉ በሥራ ላይ ባሉት በማናቸውም የግብርና የክፍያ ዓይነቶች መሠረት ሊከፈል የሚገባውን ግብር/ታክስ፣ የአገ/ክፍያ እና ኪራይ የሚገልፅ የግብር/ታክስ ውሣኔ ማስታወቂያ በደረሣቸው በ30 /በሰላሣ/ ቀናት ውስጥ ተፈላጊውን ግብር/ታክስ ያልከፈሉ ወይም በሕግ በተደነገገው መሠረት ያቀረቡት አቤቱታ ወይም ይግባኝ አግባብ ባለው አካል ታይቶ ውሣኔ ከተሠጠ በኋላ በውሣኔው መሠረት ካልተስማሙ ስልጣን ላለው ፍ/ቤት ጉዳዮን ማቅረብ ባለባቸው ጊዜ ሳያቀርቡ በመቅረት የግብር/ታክስና የኪራይ /የአገ/ክፍያ ግዴታቸውን ባልተወጡ ግብር/ታክስ የአገ/ክፍያ ከፋዮች ላይ ሁሉ ተፈፃሚነት ይኖረዋል፡፡

6. <u>የግብር/ታክስ እና የኪራይ ወይም የአገ/ክፍያ አሰባሰቡ ተግባር የሚከናወንበት አፈፃፀም፡-</u>

ንብረት በመያዝ የግብር/ታክስ፣የአገ/ክፍያ እና ኪራይ አሰባሰቡ ተግባር ቀጥሎ በተመለከቱት ዓይነት ይከናወናል፡-

1. የግብር/ታክስ፣ የአገ/ክፍያ እና ኪራይ ባለዕዳውን የሚንቀሣቀስ ንብረት በማስከበር፣ በመያዝ እና በመሸጥ፣
2. የግብር/ታክስ እና የኪራይ ወይም የአገ/ከፍያ ባለዕዳውን የማይንቀሣቀስ ንብረት በማስከበር በመያዝ እና በመሸጥ፣
3. የግብር/ታክስ»እና የኪራይ ወይም የአገ/ከፍያ ግዴታውን ያልተወጣው ሰው ንብረት በእጁ የሚገኝ ወይም ለግብር ከፋዩ ማናቸውም ግዴታ ያለበት ሰው ግብር አስገቢው መ/ቤት የያዘውን እንዲያስረክብ ወይም ያለበትን ግዴታ እንዲፈፀም በማድረግ ነው፣
4. የግብር/ታክስ» እና የኪራይ ወይም የአገ/ከፍያ ባለዕዳውን የንግድ ሥራ ሀብቶች ጨምሮ የሚንቀሣቀሱና የማይንቀሣቀሱ ንብረቶች የማስተዳደሩ ተግባር የሚከናወነው ተረካቢ በመመደብ ነው።

7. <u>የግብር/ታክስ »**እና የኪራይ ወይም የአገ/ክፍያ** አስገቢው ባለስልጣን **/መ/ቤት/ከተማ ሥራ አስኪያጅ** ስልጣንና ተግባር፡-</u>

1. የግብር/ታክስ» አሰባሰቡን የሚያደናቅፍ ሁኔታ መኖሩን ሲረዳ የግብር/ታክስ ውሳኔ ማስታወቂያ ከተላከ በኋላ መቆየት ያለበትን የሰላሣ ቀናት ጊዜ ገደብ ሣይጠብቅ በአፋጣኝ ንብረቱን የመያዝ እርምጃ እንዲወሰድ ያደርጋል፣
2. በግብር/ታክስ፣የአገ/ክፍያ እና ኪራይ ዕዳ ምክንያት የሚያዙ ንብረቶች ማቆያ /ማከማቻ/ ቦታና የጥበቃ አገልግሎት ከመንግሥታዊ እና ሌሎች አካላት መገኘቱን ይከታተላል፣
3. በግብር/ታክስ፣የአገ/ክፍያ እና ኪራይ ዕዳ ምክንያት የተያዘ ንብረት ግምት የሚያከናውኑ ክፍሎች /አካላት/ የግምቱን ሥራ በወቅቱና በአግባቡ ስለማከናወናቸው ይከታተላል፣
4. አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የንብረት መያዝና መሸጥ አፈፃፀም እንዲቆም ያደርጋል፣
5. በግብር/ታክስ፣የአገ/ክፍያ እና ኪራይ ዕዳ ምክንያት የተያዘ ንብረትን አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ተማክሎ የሚሸጥበትን ዘዴ ሊወሰን ይችላል፣

6. አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በግብር/ታክስ ዕዳ የተያዙ የግብር/ታክስ፣የአገ/ክፍያ እና ኪራይ ከፋዩ ንብረቶች አስተዳደር በሌሎች አካላት ስለሚከናወንበት ሁኔታ ይፈቅዳል፡፡

7. በዚህ አንቀፅ 7 ከንዑስ አንቀፅ 1 እስከ 6 ለባለሥልጣን መ/ቤቱ ዋና ዳይሬክተር የተሰጡ ኃላፊነቶች በከተማ አስተዳድር ከተሞች በደንቡ ተለይቶ በተሰጣቸው የገቢ መሠረቶችን አስመልክቶ ለሚነሱ ጉዳዮች ላይ የከተማው ከንቲባ ጽ/ቤት ስልጣን ይሆናሉ፡፡

8. በዚህ አንቀፅ 7 ከንዑስ አንቀፅ 1 እስከ 6 ለባለሥልጣን መ/ቤቱዋና ዳይሬክተር የተሰጡ ኃላፊነቶች በማ/ቤት ደረጃ ባሉ ከተሞች በደንቡ ተለይቶ በተሰጣቸው የገቢ መሠረቶችን አስመልክቶ በሚነሱ ጉዳዮች ላይ የመ/ቤቱ/ምክር ቤቱ ስልጣን ይሆናሉ፡፡

8. <u>የግብር/ታክስና የኪራይ የአገ/ክፍያ አሰባሰብ ተግባር የሚከታተል የከተማ አስተዳደር እና የወረዳ ገቢዎች ጽ/ቤት ኃላፊዎች ሥልጣንና ተግባር፡-</u>

የግብር/ታክስና ኪራይ የአገ/ክፍያ አሰባሰብ የሚከታተል የከተማ/ወረዳ አስተዳደር ገቢ ጽ/ቤት ኃላፊ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፡፡

1. የግብር/ታክስ»፣የአገ/ክፍያ እና ኪራይ  አሰባሰቡን የሚያደናቅፍ ሁኔታ መኖሩን ሲረዳ የግብር/ታክስ ውሳኔ ማስታወቂያ ከተላከ በኋላ መቆየት ያለበትን የሰላሣ ቀናት ጊዜ ገደብ ሣይጠብቅ በአፋጣኝ ንብረቱን የመያዝ እርምጃ ይወስዳል፡፡

2. በግብር/ታክስ»፣የአገ/ክፍያ እና ኪራይ  ዕዳ ምክንያት ንብረት ስለማስከበር እና የሐራጅ ሽያጭ የሚመለከቱ ማስታወቂያዎችን ያስወጣል፡፡

3. የንብረት መያዝ፣ ማስከበር የንግድ ድርጅት ማሸግ ተግባሮችን አፈፃፀም ድጋፍ የሚሰጡ የፖሊስ አካላት፣ የቀበሌ አስተዳደር ተወካዮች እንዲገኙ እንደአስፈላጊነቱ በደብዳቤ ጥሪ ያደርጋል፡፡

4. በግብር/ታክስ»፣የአገ/ክፍያ እና ኪራይ ዕዳ ምክንያት ባለሥልጣኑ በከተማ አስተዳደሩ ይዞታ ሥር እንዲሆን የተወሰነ ተንቀሣቃሽ ንብረት፣ ወደ የንብረቱ ማቆያ/ማከማቻ ቦታ እንዲጓጓዝ ያደርጋል፡፡ የማይንቀሣቀስ ንብረት የንግድ ሥራ የሚያካሂድበትን ጨምሮ ባለበት ተከብሮ እንዲቆይ ወይም እንዲታሸግና ጥበቃ እንዲመደብለት መደረጉን ይከታተላል፡፡

5. ንብረቱ ሊያዝበት በሂደት ላይ ያለ ወይም ንብረቱ የተያዘበት ግብር/ታክስ» የኪራይ የአገ/ክፍያ ከፋይ የግብር/ታክስ ዕዳው ክፍያ ጊዜ እንዲሰጠው ወይም

በየጊዜው በሚደረግ ክፍያ ለመፈፀም እንዲፈቀድለት በሚያቀርበው ማመልከቻ ላይ ውሣኔ ይሠጣል፡፡

6. በሐራጅ ለመሣተፍ የሚፈልጉ በሐራጅ የሚሸጠውን ንብረት በቦታው ተገኝተው ማየት እንዲችሉ ንብረቱ የሚገኝበት ቦታ በሥራ ሰዓት ለተመልካቾች ክፍት መደረጉን ይከታተላል፡፡

7. በግብር/ታክስ» የአገ/ክፍያ ዕዳ ምክንያት የተያዙ ንብረቶች የተሻለ ጥቅም የሚያስገኙና አፈፃፀማቸውን ቀላል የሚሆንበትን ሁኔታ መሠረት በማድረግ በአንድ ጊዜ ወይም በቅደም ተከተል ከፍተኛ ጠቀሜታ ባለውና አመቺ በሆነ ሕጋዊ ሽያጭ እንዲሸጡ ይደረጋል፡፡

8. በግብር/ታክስ» የአገ/ክፍያ ዕዳ ምክንያት የተያዘ ንብረት የሐራጅ ሽያጭ ሪፖርት መቅረቡን ይከታተላል፡፡

9. በሐራጅ የተሸጠ ንብረት አሸናፊ ቀሪ ክፍያውን በወቅቱ ለባለስልጣኑ ለከተማው አስተዳደር ወይም ለማቤቱ ገቢ ስለማድረጉ ይከታተላል፡፡

10. የግብር /ታክስ፣ የአገ/ክፍያ ባለዕዳው ንብረት በሐራጅ ተሸጦ የሚገኘው ገቢ እንደየ ዕዳቸው መጠን ለከተማ አስተዳደሩና ለገቢዎች ባለስልጣን በየሂሳብ ኮዳቸው በማከፋፈል ፈሰስ ያደረጋል፡፡

11. በሐራጅ የተሸጠ ንብረት ዋጋ ሙሉ በሙሉ መከፈሉን በማረጋገጥ የንብረቱ ባለቤትነት በገዢው ስም እንዲዛወር ለሚመለከተው የመንግሥት አካል ደብዳቤ ይጽፋል፡፡

12. በሁለተኛና ከዚያ በኋላ በተደረጉ ሐራጅ ያልተሸጡ ባለሥልጣኑ የከተማ አስተዳደሩ/ማ/ቤቱ በዓይነት፣ በመጠን ወይም በቁጥር የሚረከበውን ንብረት ርክክብ መፈፀሙን ይከታተላል፡፡

13. በግብር/ታክስ»፣የአገ/ክፍያ ዕዳ ምክንያት የተያዙ ንብረቶችን በሚመለከት በማናቸውም ደረጃ ለሚቀርብ ጥያቄና አቤቱታ ተገቢው የሕግ ክርክር መደረጉን ይከታተላል፡፡ የሕግ መተላለፍ ተግባራትን ለሕግ እንዲቀርቡ ያደርጋል፡፡

14. በአንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ 4 እና 5 የተገለፁትን እንደ አግባብነታቸው ይፈፅማል፡፡

15. በግብር/ታክስ»፣የአገ/ክፍያ ዕዳ ምክንያት ከንብረት መያዝ፣ ማስከበር መሸጥ ጋር የተያዙ በገቢዎች ባለሥልጣን ዋና ዳሬክተር የከተማ አስተዳደሩ ከንቲባ

እንዲሁም እንደየአግባብነቱ ከወረዳ አስተዳድሩ የሚሠጡትን ሌሎች ተግባሮችን ያከናውናል፡፡

## ክፍል ሁለት

## የግብር ባለዕዳውን ሀብት በማስከበር ስለመያዝ፣

9. ንብረትን ስለማስከበር የሚሰጥ ማስታወቂያ፡–

1. ንብረት ለማስከበር የሚሰጥ ማሰታወቂያ የግብር ሰብሳቢው መ/ቤት ባለሙያዎች በአካል ተገኝተው ድርጅቱን ከማሸጋቸው ወይም ንብረቱን/ሃብቱን ከመያዛቸው በፊት እንዳይንቀሳቀስ ለግብር/ታክስ ፣የአገ/ ክፍያ ባለዕዳው የሚሰጥ ማስታወቂያ ነው፡፡

2. ንብረት ስለማስከበር የሚሰጠው ማስታወቂያ ቀጥሎ የተዘረዘሩትን ማካተት አለበት፡፡

ሀ/ የከተማ/የወረዳ አስተዳደሩ ቀደም ሲል ለግብር/ታክስ ከፋዩ የተላኩለት የግብር/ታክስ ውሣኔ ማስታወቂያ ቀን እና ቁጥር፣

ለ/ ከግብር/ታክስ ከፋዩ የሚፈለገው የግብር/ታክስ የኪራይ የአገ/ክፍያ ዕዳ፡–

- ፍሬ ግብር/ታክስ፣ የአገ/ክፍያ
- ማስታወቂያው እስከተላከበት ጊዜ ድረስ የታሰበው ወለድ፣
- መቀጫ፣
- አስቀድሞ የተከፈለው ተቀናሽ የተደረገ መሆኑን እና
- በቀሪነት የሚፈለገውን ግብር/ታክስ/፣

ሐ/ የከተማ አስተዳደሩ የግብር/ታክስ ከፋዩን ንብረት/ሀብት በመሸጥ ከሽያጩ የሚያገኘውን ገንዘብ ለግብር/ታክስ ዕዳው ብቻ ሣይሆን ንብረቱን ከመሸጥ ጋር በቀጥታ ለተያያዙ የአፈፃፀም ተግባሮች ማከናወኛ ለሚወጣው ወጪ ጭምር መሸፈኛ የሚያውለው መሆኑን የሚገልፁ መረጃዎች መያዝ አለበት፡፡

3. ንብረት ለማስከበር የሚሰጥ ማስታወቂያ ለግብር/ታክስ ባለዕዳው ለመስጠት ተፈልጐ ካልተገኘ ወይም ለመቀበል ፈቃደኛ ካልሆነ በግብር/ታክስ ከፋዩ ወይም ወኪሉ ወይም የንግድ ሥራ ማከናወኛ ቦታው ወይም መኖሪያ ቤቱ ላይ ወይም መስሪያ ቤቱ ወይም አመችና ግልጽ ሆኖ በሚታይ ስፍራ እንዲለጠፍ በማድረግ ድርጅቱን የማሸግ ወይም ንብረቱን/ሃብቱን በቁጥጥር

ስር አድርጐ እንዳይንቀሳቀስ የማድረግ ሥራዎችን አከታትሎ ወዲያውኑ ያከናውናል፡፡

10. <u>ንብረት ለማስከበር ማስታወቂያ ከመፃፉ በፊት ስለሚከናወኑ ተግባራት፡-</u>

1. የግብር፣ የአገ/ ክፍያ አስገቢው የግብር ውሣኔ ማስታወቂያ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ወይም በአቤቱታ አጣሪ ባለሙያዎች ወይም ይግባኝ ቀርቦ በግብር ይግባኝ ጉባዔ ውሣኔ ከተሠጠበት ቀን ጀምሮ ባሉት 30 ቀናት ውስጥ ለሚፈለግበት የግብር/ታክስ ዕዳ የግብር ባለዕዳውን ሀብትና ንብረት እንቅስቃሴ የሚመለከት መረጃ ማሰባሰብ አለበት፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት የሚሰበሰበው መረጃ የግብር ባለዕዳውን ሀብት ዓይነት፣ ብዛት፣ የሚገኝበትን አድራሻ፣ የባለሀብትነቱን ዓይነት በማን ይዞታ ሥር እንደሚገኝ፣ በዋስትና የተመዘገበ መሆን አለመሆኑን የመሳሰሉ መረጃዎችን የሚጨምር መሆን አለበት፡፡
3. በተሰበሰበው መረጃ ወይም በተገኘ ጥቆማ መሠረት የግብር አስገቢው የከተማ አስተዳደሩ በአንቀጽ 7 እና 8 የተገለጹት ኃላፊዎች የግብሩን አሰባሰብ የሚያደናቅፍ ሁኔታ መኖሩን የተረዳ ወይም የተገነዘበ እንደሆነ እና ለመክፈል ፈቃደኛ አለመሆኑን/በመረጃ ከተደረሠበት ወይም ከታወቀ የግብር መክፈያ ጊዜውን ሰላሣ ቀናት ሣይጠብቅ ንብረቱን በመያዝ ግብር የመሰብሰቡ አፈፃፀም እንዲካሄድ ትዕዛዝ ይሰጣል፡፡
4. ንብረቱ እንዲከበር የሚሰጠው ትዕዛዝ ለግብር ባለዕዳው፣ ተቀጣሪ፣ የግብር ባለዕዳው ሃብት በእጁ ወይም በይዞታው ለሚገኝ ለማናቸውም ሰው፣ እንደሁኔታው ንብረትን ወይም መብትን ለሚመዘግብ አግባብ ያለው ሰው፣ ፍርድ ለሚያስፈጽም....... ወዘተ መስጠት አለበት፡፡

11. <u>ንብረትን ስለማስከበር፡-</u>

1. የግብር አስገቢው መ/ቤት ወይም የከተማ አስተዳደሩ ንብረቱን ለማስከበር ሲንቀሳቀስ ወዲያውኑ የግብር ከፋዩ ሀብትና ንብረት በዋስትናነት እንደተሰጠ ንብረት ሣይሸጥ፣ ሣይለወጥ፣ ሣይከፈል፣ ባለሀብትነትም ሆነ ይዞታ ሣይዛወር ተከብሮ እንዲቆይ እንዲያደርግ ለራሱ ለግብር ከፋዩ እና ንብረት ወይም መብት ወይም ድርሻ ለሚመዘግብ አግባብ ያለው የመንግሥት አካል ወይም የግል ድርጅት፣ ወይም የግብር ከፋዩ ሀብት በእጁ ለሚገኝ ሰው ማስታወቂያ ይልካል፡፡
2. ንብረት ተከብሮ እንዲቆይ የሚሠጥ ማስታወቂያ ይዘት ከዚህ መመሪያ ጋር በተያያዘው አባሪ የተዘረዘሩትን መረጃዎች የያዘ መሆን አለበት በድርጅቱ ውስጥ

የሚገኝ ንብረት እንዳይሸሽ ድርጅቱ እንዲቆለፍ ተደርጐ በገቢ ሰብሳቢ መ/ቤት የተከበረ መሆኑን ማስታወቂያ ይለጥፋል።

3. ንብረት ወይም መብት ወይም ድርሻን የሚመዘግበው አካል በግብር ከፋዩ ስም የተመዘገበ ንብረት ወይም መብት ወይም ድርሻ ተከብሮ እንዲቆይ ማድረግና የተከበረውን ንብረት ዓይነት ለግብር/ለታክሱ ባለስልጣን ወይም እንዳስፈላጊነቱ ለከተማ አስተዳደሩ ማስታወቅ አለበት።

4. የግብር ከፋዩ ንብረት ወይም ሀብት በእጁ የሚገኝ ማናቸውም ሰው ንብረት የማስከበሩ ማስታወቂያ ባይደርሰው ኖሮ ንብረቱን ለግብር ከፋዩ የሚያስረክብ መሆኑንና ንብረቱ በእጁ ወይም በይዞታው እንዲቆይ መደረጉ ወጭ ያስከተለበት መሆኑን በበቂ ማስረጃ አስደግፎ ያቀረበ እንደሆነ የዚህ አይነቱ ወጭ የግብር ከፋዩን ሃብት በመያዝና በመሸጥ እንደወጣ ወጪ ተቆጥሮ ከንብረቱ ሽያጭ ከተገኘ ገቢ ላይ እንዲከፈለው ይደረጋል።

12. <u>ስለማይከበሩና ስለማይያዙ ሀብቶች፡-</u>

ከዚህ በታች የተመለከቱት ንብረቶች በግብር ዕዳ ምክንያት የማይከበሩ እና የማይያዙ ናቸው።

1. ለግብር ባለዕዳውና ለቤተሰቡ የዕለት አገልግሎት የሚያስፈልጉ ልብሶች የምግብ ማብሰያ የሆኑ የቤት ቁሣቁሶች፣ አልጋ፣ የአልጋ ልብስ ፍራሽ፣ ትራስ እና ብርድ ልብስ፣
2. ለሙያው ሥራ አስፈላጊ የሆኑ የእጅ መሳሪያዎች፣
3. የግብር ባለዕዳው በግብርና ሥራ የሚተዳደር ከሆነ በግብር ሰብሣቢው አካል አስተያየት ለሥራው አገልግሎት በቂ ሆነው የሚገመቱ የቀንድ ከብቶች፣ የጋማ ከብቶች፣ የዘር እህልና ሌላም ፍፁም አስፈላጊ ነገሮች፣
4. ለግብር ባለዕዳውና ለቤተሰቡ ለሶስት ወራት መተዳደሪያ የሚሆን ገንዘብ ወይም ቀለብ፣
5. የግብር ባለዕዳው የሚከፈለው የጡረታ ገንዘብ ባል/ሚስት ለሚስቱ/ለባልዋ ከፍቺ በኋላ ለቀለብ የሚከፍሉት ገንዘብ
6. በሠንጠረዥ «ሀ» ከግብር ነፃ ከተደረገው የገቢ መጠን ሳያልፍ ሰራተኛው የሚያገኘው ደመወዝ ወይም ማናቸውም በተወሰነ ጊዜ የሚገኝ ሌላ ገቢ፣
7. የባልና ሚስት የቃል ኪዳን ቀለበት፣ ሜዳሊያ/ ኒሻን፣
8. እንዳይከበር እንዳይሸጥና ለዕዳ መክፈያ እንዳይሆን በማናቸውም ሌላ ሕግ ላይ የተወሰነ ማናቸውም ዓይነት ሀብት ወይም ንብረት፣

9. የጠበቆች፣ የሀኪሞች እና የአካውንታንቶች/አዲተሮች ፋይሎችና ሠነዶች ነገር ግን የግል ወይም የሙያ ጉዳዮችን ፋይሎች የያዘ ኮምፒዩተር በተያዘ ጊዜ መከተል ስለሚገባው የአፈፃፀም ሥርዓት የግብር ሰብሣቢው ባለስልጣን መ/ቤት የከተማ አስተዳደሩ ከንቲባ የበላይ ኃላፊ ውሣኔ ይሠጣል፡፡

10. መያዝ መሸጥና መዘዋወር በሕግ ክልከላ የተደረገባቸው ዕቃዎች ለመያዝ፣ ለመጠቀም ወይም ለመሸጥ ልዩ ፈቃድ የሚያስፈልጋቸው ዕቃዎች የሚወረሱ ወይም ኮንትሮባንድ የመጠቀሚያ ጊዜ ያለፈባቸው ወይም የተሠረቁ ዕቃዎች ከተገኙ አግባብ ያለውን አካል በማሣወቅ እንዲረከቡ በማድረግ ወይም አስፈላጊው እርምጃ እንዲወሰድ መደረግ አለበት፡፡

13. <u>ንብረት መያዝ</u>፡-

1. የግብር ውሳኔው በደረሰው በ30 ቀናት ውስጥ ካልከፈለ ወይም በግብር አስገቢው ባለስልጣን ዘንድ ቀርቦ የመክፈያ ጊዜ እንዲሰጠው ያላደረገ ወይም በአንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ 7- 4 መሠረት በበቂ ዋስትና የተደገፈ ስምምነት ላይ ካልተደረሰ፣ በአንቀጽ 12 ከመያዝ ነፃ ከተደረጉት ወይም በፍ/ቤት አስቀድሞ ከተከበረ ወይም በዋስትና ከተያዘ ንብረት በስተቀር ማናቸውንም የግብር ባለዕዳውን ንብረት የግብር አስገቢው የከተማ አስተዳደሩይይዛል፣ ለግብር ዕዳው መክፈያ እንዲውል ያደርጋል፡፡

2. ለግብር/ታክስ ዕዳ ክፍያ የሚያዘው ንብረት ዋጋ በተቻለ መጠን ከግብር/ታክስ ዕዳው ዋጋ ጋር ተመጣጣኝ መሆን አለበት፡፡

3. የግብር አስገቢው/የከተማ አስተዳደሩ ንብረት ከመያዙ በፊት ንብረቱ እንዲከበርና እንዲያዝ የተሠጠውን ውሣኔ /የትዕዛዝ ቅጂ ለዚህ መመሪያ በአንቀጽ 10(4) ለተገለፁት አካላት ሁሉ ይሠጣል፡፡

4. ከእርሻ ሰብል በስተቀር

ሀ/ ማናቸውም የሚንቀሣቀስ ንብረት የሚያዘው በግብር ባለ ዕዳው እጅ የሚገኘውን ንብረት በመረከብ ነው፡፡ የገቢ አሰባሰብ ክትትል ባለሙያዎች ንብረት በሚይዙበት ወቅት እርዳታ የሚያስፈልጋቸው ከሆነ የፖሊስ ኃይል እንዲገኝ ማድረግ ይችላሉ፡፡ ግብር ከፋዩ ከሁለት ያልበለጡ እማኞች ሊያቀርብ ይችላል፡፡ የገቢ አሰባሰብ ክትትል ባለሙያዎች የግብር ባለዕዳው ወይም ወኪሉ በተገኙበት ንብረቱን ቆጥሮና መዝግቦ በእማኞች ፊት ይረከባል፣ በቦታው የተገኙት ሁሉ ይህንኑ በፊርማቸው ያረጋግጣሉ፡፡

ለ/ የግብር አሰባሰብን የሚከታተሉ ባለሙያዎች የተረከቡትን ንብረት በሚገባ ለመጠበቅና አጠባበቁም ለሚጠይቀው ጥንቃቄ ሁሉ ኃላፊነት አለባቸው፡፡

የተቆጠረው ንብረት ዝርዝር ተረካቢው ገቢዎች ጽ/ቤት እና የተገኙት ሰዎች ከፈረሙበት በኋላ አንዱ ቅጂ ለግብር ባለዕዳው ይሠጣል፡፡

ሐ/ የተያዘው ንብረት የተከበሩ ማዕድናት ማለት አልማዝ፣ ዕንቁ፣ ወርቅና ብር.... ወዘተ የሆነ እንደሆነ መጠኑ በሚዛን ተመዝኖና ዋጋው በባለሙያ ተገምቶ ይኸው ሁኔታ በዝርዝሩ ላይ መገለፅ አለበት፡፡

5. የተያዘው ወይም የተከበረው ንብረት በቶሎ የሚበላሽ፣ በስብሶ ዋጋ የሚያጣ ወይም ለጥበቃው የሚያስፈልገው ወጪ ከዕቃው ዋጋ የሚበልጥ የሆነ እንደሆነ የግብር አሰባሰቡን የሚከታተል የከተማ አስተ/የገቢዎች ጽ/ቤት ኃላፊ ወይም የወረዳ ገቢዎች ጽ/ቤት ኃላፊ ወዲያውኑ እንዲሸጥ ውሣኔ ሊሠጥ ይችላል፡፡

6. የሚያዘው ወይም የሚከበረው ሀብት የእርሻ ሰብል ወይም ዛፍ/ፍሬ የሆነ እንደሆነ በማሣው ላይ ተያይዞ ያለ ከሆነ ትዕዛዙን በሥፍራው በመለጠፍ፣ ሰብሉ ታጭዶ የተከመረ ወይም በመወቃት ላይ ያለ የእንሰሳት መኖ ክምር ሲሆን፣ በክምሩ ወይም በአውድማቸው አቅራቢያ በመለጠፍ የሚፈፀም ሲሆን የትዕዛዙ ቅጂ በግብር ባለዕዳው መኖሪያ ቤት እና በሌላ በግልፅ በሚታይ ሥፍራ ይለጠፋል፡፡

7. በንዑስ አንቀጽ (6) የተከበረው ንብረት ስለሚጠበቅበት ሁኔታ የግብር አሰባሰቡን የሚከታተል ገቢዎች ኃላፊ የተሰጠው ትዕዛዝ እንደተጠበቀ ሆኖ የግብር ባለዕዳው ሰብሉን ሊያጭድ፣ ሊወቃ ይችላል፡፡ የግብር ባለዕዳው ይህን ባላደረገ ወይም ፈቃደኛ ባልሆነ ጊዜ በግብር ባለዕዳው ላይ በሚታሰብ ወጪ ሊታጨድ ሊወቃ ይችላል፡፡

8. እንዲያዝ ወይም እንዲከበር የታዘዘው ሀብት እና ንብረት ወይም መብት በግብር ባለዕዳው እጅ ያልገባ ከሌላ ሰው የሚጠይቀው በሚተላለፍ ሠነድ ያልተደገፈ ገንዘብ፣ ወይም በፍርድ ቤት ክሶ በማስፈረድ መብት ያገኘበት ገንዘብ ወይም ሌላ ሀብት በሆነ ጊዜ የግብር አስገቢው ባለሥልጣን ኃላፊ የከተማ አስተዳደሩ ከንቲባ ሌላ ግልፅ የሆነ ትዕዛዝ እስኪሰጥ ድረስ ሀብቱ ወይም ገንዘቡ በእጅ ያለ ሰው ገንዘቡን ወይም ሀብቱን ወይም መብቱን ለግብር ባለዕዳውም ሆነ ለሌላ ሰው ማይሠጥ/ሳያስተላልፍ በእጁ እንዲያቆይ በጽሑፍ ማዘዝ ይኖርበታል፡፡ ሀብቱ በንግድ ማህበር የተመዘገበ የአክስዮን ሰነድ የሆነ እንደሆነ ሰነዱን የግብር ባለዕዳው ለሌላ ሰው እንዳይሠጥ እንዳይሸጥ ወይም የትርፍ ድርሻውን እንዳይቀበል በማድረግና የንግድ ማህበሩም የሠነዱን ዝውውር በሌላ ሰው ስም እንዳይመዘገብ በትዕዛዙ ውስጥ በግልፅ በማመልከት ይፈፀማል፡፡ የትዕዛዙ ቅጂ በግብር አስገቢው ቅጥር ግቢ በግልፅ በሚታይ ሥፍራ ይለጠፋል፡፡ ገንዘቡ፣ ሀብቱ ወይም ሠነዱ በእጁ የሚገኝና ትዕዛዙ የደረሠው ማናቸውም ሰው ሃብትና ንብረቱ ወይም ሠነዱን በደረሰኝ ለግብር አስገቢው መክፈል ወይም ማስረከብ አለበት፡፡

9. የሚከበረው እና የሚያዘው ንብረት የግብር ባለዕዳው ከሌሎች ሰዎች ጋር በተከፋይነት ወይም በጋራ የሚጠቀምበት ወይም የጋራ ባለሀብት የሆነበት ሀብት ወይም በሽርክና የያዘው ሀብት ሲሆን የመያዙ ወይም የማስከበሩ ሥርዓት የሚፈፀመው ድርሻውን ለሌላ ሰው አሣልፎ እንዳይሰጥ፣ እንዳይሸጥ፣ በዋስትና እንዳያስይዝ ወይም በማናቸውም ምክንያት እንዳያስተላልፍ ከሽርክናው የሚገኘውን ትርፍ እንዳይወስድ የማገድ ትዕዛዝ ለጋራ ባለሀብቶቹ ወይም ለሸሪኮቹ በመስጠት ነው፡፡ የትዕዛዙ ቅጂ ለግብር ባለዕዳውም መሰጠት አለበት፡፡

10. የሚያዘው ሀብት የግብር ባለዕዳው የሚያገኘው ደመወዝ ሲሆን በየወሩ እየተቀነሰ ወይም የግብር አስገቢው ባለልጣን በሚያዘው ሁኔታ እንዲያዝ ይደረጋል፡፡ የማንኛውም ሠራተኛ ደመወዝ እንዲያዝ የሚሰጠው ትዕዛዝ ከሠራተኛው የሚፈለገውን የግብር ዕዳ መጠን የሚገልፅ መሆን አለበት፡፡ ትዕዛዙ የደረሰው ቀጣሪም በየወሩ ከደመወዙ ላይ እየቆረጠ ለግብር አስገቢው ባለሥልጣን መክፈል አለበት፡፡ እንዲያዝ የታዘዘው የደመወዝ ድርሻ መጠን በፍርድ ቤት ወይም በሌላ የግብር አስገቢው አካል በተሰጠ ትዕዛዝ ምክንያት አስቀድሞ የተያዘ ሲሆን ሁለተኛው ትዕዛዝ የደረሰው ቀጣሪ ይህንኑ በመግለፅ ቀደም ሲል የደረሰውን የትዕዛዝ ግልባጭ ከመግለጫ ጋር በማያያዝ ለግብር ሰብሳቢው ባለሥልጣን ለከተማ አስተዳደሩ መልሶ መላክ ይኖርበታል፡፡ በተጨማሪም ሠራተኛው የደመወዝ ጭማሪ ባገኘ ጊዜም ሆነ መ/ቤቱን በለቀቀ ጊዜ ወዲያውኑ ለግብር አስገቢው ባለሥልጣን ለከተማ አስተዳደሩ ማሣወቅ አለበት፡፡ ከግብር ባለዕዳው ደመወዝ ላይ በየጊዜው የሚቆረጠው የገንዘብ መጠን በባለሥልጣኑ በከተማ አስተዳደሩ ትዕዛዝ ላይ መገለጽ አለበት፡፡

11. እንዲያዝ የታዘዘው ሀብት የሚዘዋወር የገንዘብ ሰነድ የሆነ እንደሆነ እና በፍርድ ቤት ወይም በመንግሥት መሥሪያ ቤት ያልተያዘ ከሆነ የማስከበሩ ወይም የማስያዙ ሥርዓት የሚፈፀመው ተዘዋዋሪ የገንዘብ ሰነድ ተይዞ በግብር አስገቢው ባለሥልጣን መ/ቤት ወይም በከተማ አስተዳደሩ እንዲቀመጥ በማድረግ፣ በሌላ አካል የተያዘም ከሆነ ሌላ ትዕዛዝ እስከሚሰጥ ድረስ እንዳይለቀቅ የሚያግድ ትዕዛዝ በመስጠት ይሆናል፡፡ ለአምጪው እንዲከፈል የሚሉ የማስጫኛ ሰነዶቹ እንዲያዙ እንዲሁም በሰነዶቹ የሚጠየቅ ንብረት እንዳይለቀቅ ትዕዛዝ መስጠት አለበት፡፡

12. እንዲያዝ ወይም እንዲከበር የታዘዘው ሃብትና ንብረት በፍርድ ቤት ወይም በመንግሥት መሥሪያ ቤት የሚገኝ ሲሆን ሀብቱ ራሱ ወይም የሚያስገኘው ማናቸውም ጥቅም ተጠብቆ እንዲቆይ የግብር ባለሥልጣኑ ከተማ አስተዳደሩ ትዕዛዝ በመስጠት ማስከበር ይችላል፡፡

13. የግብር ባለዕዳው በሣጥኑ ስላለው ንብረት መረጃ እንዲሰጥ ተጠይቆ ፈቃደኛ ካልሆነ ወይም ቁልፉን ለመስጠት እምቢተኛ የሆነ እንደሆነ ባንኩ ወይም የገንዘብ

ተቋሙ ቁልፉን እንዲሰጥ ተደርጐ የባንኩ ተወካይና የግብር ባለዕዳው ወይም ወኪሉ እንዲገኙ ማስታወቂያ በመስጠት ተከፍቶ በውስጡ የተገኘው ንብረት ይመዘገባል፡፡ ሌላ ውሣኔ እስከሚሰጥበት ድረስ ታሽጐ እንዲቀመጥ ይደረጋል፡፡

14. የመንግሥት ቦንድ እንዲሁም ከኢንቨስትመንት እና ከኢንሹራንስ በየጊዜው የሚከፈሉ እንዳይከፈልና ሌላ ትዕዛዝ በግብር አስገቢው ባለስልጣን በከተማ አስተዳደሩ እስከሚሰጥ ድረስ ይዞ እንዲቆይ ለሚመለከተው አካል ትዕዛዝ በመስጠት ሊከበር ይችላል፡፡

15. እንዲያዝ ወይም እንዲከበር የተወሰነው የማይንቀሳቀስ ንብረት ከሆነ የግብር ባለዕዳው ይህን ንብረት ለሌላ ሰው እንዳይሰጥ፣ እንዳይሸጥ፣ እንዳይለውጥ ወይም በማናቸውም ሌላ ሁኔታ መብቱን ለማንም ሰው እንዳያዛውር እንዲሁም ሌሎች ሰዎች በዚህ ንብረት ላይ የዋስትና መብትን ጨምሮ ማናቸውንም ዓይነት መብት እንዳይኖራቸው የሚያግድ ትዕዛዝ የማይንቀሳቀስ ንብረት ለሚመዘግበው አካል በመስጠት የሚፈፀም ይሆናል።

የትዕዛዙ ቅጂ በንብረቱ አቅራቢያ ወይም በማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ በግብር አስገቢው ባለሥልጣን በከተማ አስተዳደሩ ግቢ ውስጥ ግልፅ ሆኖ በሚታይ ሥፍራ ይለጠፋል። አንድ ቅጂ ለግብር ባለዕዳው ይሰጣል።

14. <u>የደንበኞችን ንብረት ስለመመለስ</u>፡–

የተያዘው ወይም በማሸግ የተከበረው የድርጅቱ ሳይሆን የደንበኞች ንብረት መሆኑ በበቂ ማስረጃ ሲረጋገጥ በውስጡ የሚገኝበት እንደላውንደሪ/የደረቅ እጥበት፣ ልብስ ሰፊት፣ የጥገና አገልግሎት መስጫ ወይም ጋራዥ የሆነ እንደሆን ንብረቱ ከተያዘ በኋላ ባሉት የድርጅቱ የሥራ ቀናትና ሰዓት ደንበኞች ማስረጃቸውን እያቀረቡና ያልተከፈለ የአገልግሎት ቀሪ ሂሣብ እየከፈሉ እንዲረከቡ መደረግ አለበት፡፡

15. <u>ልዩ ጥንቃቄ ስለሚያስፈልጋቸው ዕቃዎች</u>፡–

1. በዚህ መመሪያ አንቀጽ 14 በተመለከተው መሠረት ንብረት ሲያዝ በተለይ ልዩ ጥንቃቄ የሚያሻቸው ልዩልዩ ኬሚካሎች ወይም ንጥረ ነገሮች የሚሸጡባቸው፣ የሚከማቹባቸው ወይም የሚመረቱባቸው ሲሆን እነዚህን ኬሚካሎች ወይም ንጥረ ነገሮች ለመያዝ የሚያስፈልገው ጥንቃቄ በቅድሚያ መታወቅና አስፈላጊው ቅድመ ዝግጅት መደረግ አለበት፡፡

2. የዚህ ዓይነት ዕቃዎችን ለመሸጥ ወይም ለማስወገድ የሚያስፈልገው ወጪ ከሽያጩ ከሚገኘው ዋጋ እኩል የሚሆን ወይም የሚበልጥ ከሆነ ይህን ሁኔታ አስቀድሞ በመገንዘብ ሁኔታው ከታወቀበት በ15 ቀናት ውስጥ ውሣኔ ሊሠጥበት ይገባል፣

3. ስለአያያዙ፣ ስለአጠባበቁና አሻሻጡ ከሚመለከታቸው የመንግሥት አካላት ትብብር ሊጠይቅ ይችላል፡፡

16. <u>የተያዘ ወይም የተከበረ ንብረት ስለሚለቀቅበት ሁኔታ፡-</u>

የተያዘ ወይም የተከበረ ንብረት ፡-

1. ለንብረቱ መያዝ ወይም መከበር ምክንያት የሆነው የግብር ዕዳ እንዲሁም ንብረቱን ለመያዝና ለማስከበር የወጣ ወጪ በሙሉ የተከፈለ እንደሆነ፣

2. የግብር ዕዳው የተሠረዘ ወይም በምህረት እንዲቀር የተደረገ እንደሆነ፣ ወዲያውኑ ይለቀቃል፣ ንብረት/መብት ለሚመዘግቡ አካላት የመያዝ ወይም የማስከበሩ ትዕዛዝ መነሣቱ በግብር አስገቢው ባለሥልጣን ወይም በከተማ አስተዳደሩ አማካኝነት ይገለፅላቸዋል፡፡

17. <u>በተያዘ ወይም በተከበረ ንብረት ላይ የሚቀርብ አቤቱታን ስለመመርመር፡-</u>

1. የግብር ባለዕዳው የተያዘው ወይም የተከበረው ንብረት በሕግ የማይከበር ወይም የማይያዝ ነው በማለት የንብረቱ ሽያጭ ከመካሄዱ በፊት አቤቱታ ሲያቀርብለት አግባብ ያለው የከተማ/ወረዳ አስተዳደር ገቢዎች ጽ/ቤት አቤቱታውን በማጣራት ውሣኔ ይሠጣል፡፡ ውሳኔው መያዝ የለበትም የሚል ከሆነ ንብረቱ እንዲለቀቅ ይደረጋል፡፡

2. የግብር ባለዕዳው ግብር ባለመክፈሉ ምክንያት የግብር አስገቢው ባለሥልጣን የያዘው ወይም ያስከበረው ንብረት ይገባናል የሚሉ ሶስተኛ ወገኖች የሚያቀርቡትን አቤቱታ ተቀብሎ የከተማ አስተዳደር ገቢዎች ጽ/ቤት /ወረዳ የገቢዎች ጽ/ቤት ኃላፊ ይመረምራል፡፡ አስፈላጊውን ውሣኔ ይሰጣል፡፡ ንብረቱ አላግባብ የተያዘ መሆኑን እና የአቤቱታ አቅራቢው ንብረት መሆኑን በበቂ ማስረጃ በማያጠራጥር ሁኔታ ያረጋገጠ እንደሆነ የተያዘው ንብረት እንዲለቀቅ ውሣኔ ይሰጣል፡፡

18. <u>በሌላ ሰው እጅ የሚገኝን ንብረት/ገንዘብ ለመቀበል የማይቻልባቸው ሁኔታዎች፡-</u>

1. በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 76/94 አንቀጽ 79 (2) የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ የግብር ባለዕዳው ሃብት በእጅ የሚገኝ ሰው የማቻቻያ ጥያቄ በፍትሐብሄር ሕግ ከቁጥር 1831-1841 ባሉት ድንጋጌዎች መሠረት የማቻቻሉ ጥያቄ ተቀባይነት ያለው መሆኑን የከተማ ወይም የወረዳ አስተዳደር ገቢዎች ጽ/ቤት ኃላፊ ማጣራት ይኖርበታል፡፡ የመያዝ ወይም የማስከበሩ ትዕዛዝ ከደረሰው በኋላ የመክፈያ ጊዜው ለደረሠ ዕዳ በማቻቻያነት ለማዋል የሚቀርበው ጥያቄ ተቀባይነት የለውም፡፡

2. የግብር ባለዕዳው ሀብት ወይም ገንዘብ በእጁ የሚገኝ ሰው ሀብቱን ወይም ገንዘቡን ለግብር አስገቢው ባለሥልጣን ወይም ከተማ አስተዳደር ለማስረከብ ወይም ለመክፈል የማይገደድበት ሕጋዊ ምክንያት ያለው መሆኑን በመግለጽ እንቢተኛ የሆነ እንደሆነ እና ምክንያቱ በግብር አስገቢ መ/ቤት ዘንድ ተቀባይነት ያላገኘ እንደሆነ የግብር ባለስሥጣኑ ከተማ አስተዳደሩ በፍ/ቤት ክስ በማቅረብ ሃብቱን ወይም ንብረቱን ለመረከብ ይችላል፡፡

19. <u>ገንዘብ በተያዘ ጊዜ ደረሰኝ ስለመስጠት፡-</u>

የግብር ባለዕዳው በተሰጠው የመክፈያ ጊዜ ውስጥ ዕዳውን አጠናቆ ባለመክፈሉ በሚሰጥ የመያዝ ትዕዛዝ መሠረት ከግብር ባለዕዳው እጅ መኖሪያ ቤት ወይም ንግድ ወይም ሥራውን ከሚያከናውንበት ቤት እንዲሁም ከባንክና ከማንኛውም ለግብር ባለዕዳው ገንዘብ የመክፈል ግዴታ ካለበት ሰው ላይ ገንዘብ የተያዘ እንደሆነ ገቢ ለተደረገው ገንዘብ ደረሰኝ በመስጠት ከግብር ዕዳው ላይ ሂሣቡ እንዲቀነስ ይደረጋል፡፡

20.<u>ንብረትን በመያዝ ለግብር ዕዳ መክፈያ ማዋልን በውክልና ስለማስፈፀም፡-</u>

1. የግብር ባለዕዳው ሀብት ንብረት የሚገኘው የግብር አስገቢው ባለስልጣን ወይም ከተማ አስተዳደር ከሚገኝበት ክልል ውጪ ሆኖ ሲገኝ የግብር ባለዕዳው ሀብት እንዲያዝ ወይም እና እንዲከበር የተሰጠውን ውሣኔ ከአስፈላጊ ሰነዶች ጋር ሀብቱ በሚገኝበት አካባቢ ክልል ወይም ከተማ አስተዳደር ኃላፊነት ላለው ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤት በመላክ በውክልና እንዲፈፀም ሊያደርግ ይችላል፡፡

2. ሀብቱ እንዲያዝ ወይም እና እንዲከበር የተሰጠው ውሣኔና አስፈላጊው ሰነዶች ከውክልናው ጋር የደረሰው የገቢ አስገቢው ኃላፊነት ያለው አካል

ንብረቱን በመያዝና በመሸጥ ገንዘቡን እንዲያስፈፅምለት ለወከለው አካል ማስተላለፍ አለበት፡፡

## ክፍል ሶስት

## የተያዘውን የግብር ባለዕዳውን ሀብት ስለመሸጥ፣

21. ንብረት ስለመገመት፡-

1.የግብር/የታክስ ባለሥልጣኑ ከተማ አስተዳደሩ ያስከበረው፣ የያዘው ወይም ታሽጎ እንዲቀመጥ ያደረገውን የግብር/ታክስ ከፋዩን ንብረት ለመሸጥ እንዲችል ንብረቱ በታክስ ባለሠልጣነ ወይም የከተማ አስተዳደሩ ባለሙያዎች ወይም በሌሎች የንብረት ግምት ሥራ ማከናወን በሚችሉ አካላት ንብረቱ እንዲገመት ያደርጋል፡፡

2. በግብር ባለስልጣኑ በከተማ አስተዳደሩ ባለሙያዎችም ሆነ በሌሎች አካላት የሚሠራው ግምት የተጋነነ ወይም እጅግ በጣም ዝቅ ተደርጐ የተገመተ እንዳይሆን የባለስልጣኑ መ/ቤት የከተማ አስተዳደሩ የግምቱ ሥራ በአግባቡ የተሰራ መሆኑን ያረጋግጣል፡፡

3. በዚህ ዓይነት የተገመተው የሀብት ዋጋ የሐራጅ ወይም የጨረታ መነሻ ዋጋ ይሆናል፡፡

22. የንብረት አሻሻጥ ቅደም ተከተል፡-

1. የተያዘውን/የተከበረውን ንብረት ዓይነት፣ ያለበትን ቦታ፣ የንብረቱን ሁኔታ እና ሌሎች ሁኔታዎችን ከግምት ውስጥ በማስገባት የሽያጩ ዘዴ በሐራጅ ወይም በሰም በታሸገ ኤንቨሎፕ በሚቀርብ ጨረታ መሆኑን የግብር/ታ ክስ የከተማ አስተዳደር ገቢዎች ጽ/ቤት ኃላፊ ወይም የወረዳ ገቢዎች ጽ/ቤት ኃላፊ በቅድሚያ ይወስናል፡፡

2. የግብር ባለስልጣኑ ከተማ አስተዳደሩ በሐራጅ የሚሸጠው የግብር/ታክስ ከፋዩ ንብረት ከአንድ በላይ ከሆነ እንደሁኔታው ንብረቶቹ በሙሉ በአንድ ጊዜ ወይም ከፊል ንብረቶቹ በቅደም ተከተል እንዲሸጡ ለማድረግ ይችላል፡፡

3. የንብረት ሽያጭ በቅደም ተከተል የሚደረገው የከፊል ንብረቱ ሽያጭ የግብር/ታክስ ዕዳውን ለመሸፈን የማይበቃ መሆኑ እና ንብረቱን ለመሸጥ ብዙ ጊዜ የማይወስድ መሆኑ ሲታመን ነው፡፡

23. <u>የግብር/ታክስ ንብረት ሽያጭ አሰባሰብ ተግባር የተሠማሩ የሥራ ሂደቱ ሰራተኞች የወልና የግል ተግባርና ኃላፊነት፡-</u>

1. በግብር/ታክስ ዕዳ ምክንያት የተያዘ ንብረት ሽያጭ የሚከናወነው እንደአግባብነቱ በከተማ/ወረዳ ገቢዎች ጽ/ቤት ወይም በባለሥልጣኑ ዋና መ/ቤት በገቢ አሰባሰብ ክትትል ባለሙያዎች ይሆናል፣

2. የገቢ አሰባሰብ ክትትል ባለሙያዎች ሐራጅ በሚካሄዱበት ቀን የፖሊስና የቀበሌ አስተዳደር ተወካዮች የተመደበ መሆኑን እና በተገቢው ሰዓት ሐራጅ በሚካሄድበት ቦታ መድረሣቸውን ይከታተላሉ፣ ያረጋግጣሉ፣

3. ሐራጁን የሚያስቆም የፍ/ቤት ትዕዛዝ በመቅረቡ ወይም በግብር/ታክስና የአገ/ክፍያ ዕዳ አከፋፈል በተጨማሪ የጊዜ ስምምነት በመሠጠቱ ወይም ከባለስልጣኑ የበላይ ኃላፊ ሐራጅ እንዳይካሄድ ትዕዛዝ ሲሰጥ ወይም የግብር/ታክስና የአገ/ክፍያ ዕዳ ሙሉ በሙሉ የተከፈለ መሆኑን የሚያስረዱ ሰነዶች ሲቀርቡ ባለሙያዎች የሐራጅ ሽያጭ እንዳይካሄድ ያደርጋል፣

4. የግብር አሰባሰብ ክትትል ሙያተኞች ቡድን መሪው የሐራጅ ሽያጭ ሥነ-ሥርዓት አካሄዱ በቃለ ጉባዔ እንዲያዝ ያደርጋል፡፡ የቡድኑ አባላት፣ በሐራጅ የሚሸጠው ንብረት ባለቤት፣ ንብረቱ በእጁ የሚገኝ ሰው ወይም ወኪል በቃለ ጉባዔው ላይ እንዲፈርሙ ያደርጋል፡፡

5. የገቢ አሰባሰብ ክትትል ባለሙያዎች በሐራጅ የሚሳተፉ ሰዎች በሐራጅ የሚሸጠ ው ንብረት ግምት በሐራጁ ማስታወቂያ የተወሰነውን /የተመለከተውን/ ገንዘብ በቅድሚያ ማስያዛቸውን የማረጋገጥ፣ ሐራጁም በዚህ መመሪያ መሠረት በትክክል ለመካሄዱ የግልና የጋራ ኃላፊነት አለባቸው፡፡

24. <u>የሐራጅ ማስታወቂያ ስለማውጣት፡-</u>

1. በግብር ዕዳ ምክንያት የተያዘው ንብረት በሐራጅ የሚሸጠው የሐራጁ ማስታወቂያ ሰፊ ሥርጭት ባለው ጋዜጣ ላይ እንዲወጣ በማድረግ ነው፡፡

2. የሐራጅ ማስታወቂያ የንብረቱን ዓይነትና ሁኔታ፣ የንብረቱ የሐራጅ መነሻ ግምት፣ ንብረቱ የሚገኝበትን ቦታ፣ ሐራጅ የሚካሄድበትን ቀንና ሰዓት፣ የንብረቱን ባለቤት ስም፣ የሐራጅ ተካፋዮች በሐራጅ ለመሣተፍ ሊያሟሉ የሚገባቸውን ሁኔታዎች የግብር አስገቢው ባለሥልጣን ከተማ አስተዳደር ሐራጁን የመሠረዝ መብት እንዳለው የሚገልፅ መሆን አለበት፡፡

3. የሐራጅ ማስታወቂያ ከዚህ መመሪያ ጋር አባሪ በተደረገው ፎርም መሰረት መዘጋጀት ይኖርበታል፡፡

4. ማናቸውም የሚንቀሣቀስ ንብረት ሐራጅ ማስታወቂያው በጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ 15 ቀናት መቆየት አለበት፡፡ የሚሸጠው ንብረት የማይንቀሣቀስ ንብረት የሆነ እንደሆነ ሽያጩ የሚከናወነው የሐራጁ ማስታወቂያ ጋዜጣ ላይ ከወጣበት ቀን አንስቶ 15 ቀናት በኋላ ይሆናል፡፡

5. የሐራጅ ማስታወቂያ በጋዜጣ ከወጣ በኋላ ይህ የሐራጅ ማስታወቂያ ያለበትን ገፅ ፎቶ ኮፒ በማድረግ ሕዝቡ የሚሰበስብባቸው ቦታዎች በመለጠፍ በሐራጅ የሚካፈሉት ሰዎች ብዛት እንዲጨምር ጥረት መደረግ አለበት፡፡

6. በሐራጅ የሚሸጠው ንብረት ከፍተኛ ዋጋ የሚያወጣ ከሆነ በሐራጅ የሚሸጠውን ንብረት በምስል በማስደገፍ ማስታወቂያው በቴሌቪዥን እንዲተላለፍ ሊደረግ ይችላል፡፡ በቴሌቭዥን የሚተላለፈው ምስል የሚቀረፀው እንደነገሩ ሁኔታ በግብር አስገቢው ባለስልጣን ከተማ አስተዳደር የሕዝብ ግንኙነት ባለሙያ ወይም በኢትዮጵያ ቴሌቭዥን ድርጅት ወይም በሌላ የማስታወቂያ ድርጅት ሊሆን ይችላል፡፡

25. <u>ሐራጅ ስለማካሄድ፡-</u>

1. የሐራጅ ሽያጭ ሊካሄድ የሚችለው የገቢ አሰባሰብ ክትትል ባለሙያዎች ቡድን አባላት ቢያንስ ሶስቱ መገኘት አለባቸው አንድ የገቢ አሰባሰብ ክትትል ባለሙያ በሚገኝባቸው ገቢ ጽ/ቤቶች ሌሎች ባለሙያዎችን በመጨመር ከሶስት ባላነሰ ጊዜያዊ የባለሙያዎች ቡድን /ቨርቹዋል ቲም/ ተቋቁሞ እንዲሰራ ይደረጋል፡፡

2. የሐራጅ ሥነ-ሥርዓቱ ከመጀመሩ በፊት በሐራጁ የሚካፈሉ ሰዎች ስም ዝርዝር ይመዘገባል፡፡ በሐራጁ ተሣታፊዎች በሐራጅ ለመካፈል ተገቢውን መያዣ በባንክ በተመሰከረለት ቼክ ወይም በሲፒኦ ወይም በጥሬ ገንዘብ እንዲያስይዙ ይደረጋል፡፡

3. በሐራጅ ለመሣተፍ የቀረበው ሰው አንድ ብቻ ከሆነ ሐራጅ ሊካሄድ አይችልም፡፡

4. የገቢ አሰባሰብ ክትትል ባለሙያዎች የሐራጅ ሽያጭ ሥነ-ሥርዓት በመካሄድ ላይ እያለ ለሐራጁ መልካም አፈፃፀም ተቃራኒ የሆነ አድራጐቶች ከተጫራቾች በማናቸውም መልኩ ሲፈፀሙ እንደአስፈላጊነቱ ከአድራጐታቸው እንዲቆጠቡ ጥብቅ ማስጠንቀቂያ ለመስጠት ወይም ከሐራጁ ውጪ እንዲሆኑ ለማድረግ ይችላሉ፡፡

5. ሐራጁ የሚካሄደው የገቢ አሰባሰብ ክትትል ባለሙያዎች አባላት መካከል አንድ ሰው ሐራጅ ባይ በመሆንና ሐራጁን በመክፈት የሐራጅ ተሣታፊዎች የሚሰጡትን ዋጋ ለተሣታፊዎች በሚገባ በሚሰማ ሁኔታ ከ1-2 ጊዜ እየቆጠረ ተሣታፊዎች እንዲያጫርት በማድረግ ነው፡፡

6. እያንዳንዱ ተሣታፊ የሰጠው ዋጋ ከ1–2 የሚቆጠረው ተሣታፊዎች ለማሰብ ሰፊ ጊዜ እንዲያገኙ ረጋ እና ዝግ ብሎ ሲሆን፣ ሶስት ተብሎ ከተቆጠረ ሶስት ተብሎ የተቆጠረለት ሰው አሸናፊ ይሆናል፡፡ ይሁን እንጅ የሐራጅ አሸናፊ መሆኑ የሚረጋግጠው የግብር አስገቢው ባለሥልጣን ሐራጁን ሲያፀድቀው መሆኑን ለአሸናፊው ሊገለፅለት ይገባል፡፡

7. በመጀመሪያ ሐራጅ በግብር ዕዳ ምክንያት የተያዘው ንብረት ከሐራጅ የመነሻ ዋጋ በታች ሊሸጥ አይችልም፡፡

8. የግብር ባለዕዳው ወይም የጋራ ባለሀብቶች በጨረታው ለመሣተፍ አስፈላጊውን መስፈርት ካሟሉ እና ሌሎች ተጫራቾች ካቀረቡት ከፍተኛ ዋጋ እኩል ወይም በላይ በማቅረብ መሳተፍ ከፈለጉ በአንደኛ ደረጃ የግብር ባለዕዳው በሁለተኛ ደረጃ የጋራ ባለሀብቶች በቅድሚያ የመግዛት መብት ይኖራቸዋል፡፡

## 26. <u>የጨረታ አካሄድ ሥነ-ሥርዓት</u>:-

የግብር ባለሥልጣኑ ከተማ አስተዳደሩ የተያዘው ንብረት ሽያጭ በጨረታ እንዲፈፀም ከወሰነ ሽያጩ በሚከተለው አኳኋን ይከናወናል፡፡

1. የሐራጅ ማስታወቂያ በሚነገርበት አኳኋን የጨረታ ማስታወቂያ እንዲወጣ ይደረጋል፡፡
2. የጨረታ ማስታወቂያ ለመጀመሪ ጊዜ ከተነገረበት ቀን ጀምሮ በሚቆጠር የ15 ቀን ጊዜ ውስጥ ተወዳዳሪዎች የመወዳደሪያ ሀሳባቸውን ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡
3. የጨረታ መወዳደሪያ ሀሳብ ለማቅረቢያ በተወሰነው የመጨረሻ ቀን ንብረቱ የተያዘበት ግብር ከፋይ ወይም ወኪሉ በተገኘበት ጨረታው ይከፈታል፡፡
4. ለጨረታው ከቀረቡት ተወዳዳሪዎች ከፍተኛ ዋጋ የሰጠው የጨረታው አሸናፊ ይሆናል፡፡
5. የጨረታው ውጤት የፀና የሚሆነው የግብር ባለሥልጣኑ የከተማ አስተዳደሩ ከንቲባ ኃላፊየከተማ አስተዳደሩ ከንቲባ የጨረታውን ሪፖርት ሲያፀድቀው ይሆናል፡፡

## 27. <u>ሪፖርት ስለማቅረብ</u>:–

1.የገቢ አሰባሰብ ክትትል ባለሙያዎች ከዚህ መመሪያ ጋር አባሪ ሆኖ በተመለከተው ቅጽ መሠረት የጨረታውን አካሄድ የሚያሣይ ሪፖርት ያቀርባሉ፡፡

2. የሐራጁን ሪፖርት ወረዳ ገቢዎች ባለሥልጣን እና ከተማ አስተዳደር ገቢዎች ጽ/ቤቶች ከአስተያየት ጋር ለግብር/ታክስ ለከተማው ከንቲባ ባለሥልጣኑ ያቀርባሉ፡፡

28. <u>ድጋሚ /ሁለተኛ/ ሐራጅ ስለማውጣት፡–</u>

1. በግብር ዕዳ የተያዘው ንብረት በመጀመሪያው ሐራጅ ያልተሸጠ እንደሆነ የአንደኛ ሐራጅ ማስታወቂያ በወጣበት አኳኋን ድጋሜ /ሁለተኛ/ የሐራጅ ማስታወቂያ በማውጣት እንዲሸጥ ያደርጋል፡፡
2. ለድጋሚ ሐራጅ አፈፃፀም አግባብ ያላቸው የመጀመሪያ ሐራጅ ሥርዓቶች ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

29. <u>በሁለተኛ ሐራጅ ስላልተሸጠ ንብረት፡–</u>

1. በሁለተኛ ሐራጅ ያልተሸጠ ንብረት የመንግሥትን ጥቅም የሚያስጠብቅ መሆኑ የታመነበት እንደሆነ የግብር ባለሥልጣኑ ከተማ አስተዳደሩ በግምቱ ሊረከበው ወይም ሦስተኛና ከሦስተኛ በላይ ሐራጅ እንዲወጣ ሊያደርግ ይችላል፡፡
2. የግብር አስገቢው ባለሥልጣን የበላይ ኃላፊ ከንቲባው በተለየ ሁኔታ እንዲፈፀም ካልተወሰነ በስተቀር በሁለተኛ ሐራጅ ያልተሸጠው ንብረት በሶስተኛ ወይም ከሶስተኛ ጊዜ በላይ በሚካሄድ ሐራጅ ሊሸጥ የሚችለው በግምቱ ወይም ከግምቱ በላይ ብቻ ሲሆን ነው፡፡
3. ሶስተኛ ወይም ከሶስተኛ ጊዜ በላይ የሚደረግ ሐራጅ ሲካሄድ አግባብ ያላቸው የመጀመሪያ እና የሁለተኛ ጊዜ ሐራጅ ሥነ–ሥርዓቶች ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡

30. <u>ንብረት በሐራጅ ከተሸጠ በኋላ ስለሚፈፀም ተግባር፡–</u>

1. የተያዘ ንብረት በሐራጅ በተሸጠበት ቀን የሐራጅ አሸናፊ ያስያዘውን ገንዘብ በዕለቱ በልዩ ሂሳብ ለግብር አስገቢው ባለሥልጣኑ ከተማ አስተዳደሩ ባንክ ሂሳባቸው ገቢ ይደረጋል፡፡ ሌሎች ተሳታፊዎች ያስያዙት ገንዘብ ተመላሽ ይሆናል፡፡ የሐራጅ አሸናፊ ያስያዘውን ገንዘብ ለባለመብቱ በዕለቱ ገቢ ለማድረግ በበቂ ምክንያት ያልተቻለ እንደሆነ ቀጥሎ ባለው የሥራ ቀን ወደ ባለሥልጣኑ ከተማ አስተዳደሩ የባንክ ሂሳብ እንደ እዳቸው መጠን ገቢ ይደረጋል፡፡
2. የሐራጁ አሸናፊ በሐራጁ ዕለት ያልከፈለውን ቀሪ ክፍያ ሐራጁ ከተካሄደበት ዕለት ጀምሮ በሚቆጠሩ አሥራ አምስት ተከታታይ ቀናት ውስጥ ባለሥልጣኑ በከተማ አስተዳደሩ የባንክ ሂሳብ ገቢ ማድረግ ይኖርበታል፡፡
3. የሐራጁ አሸናፊ በንዑስ አንቀጽ 2 በተገለፀው ጊዜ ውስጥ ገንዘቡን ገቢ ካላደረገ የሰባት ቀን ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ በመስጠት በዚህ ጊዜ ውስጥ ካልከፈ ለገንዘቡ ለመንግሥት ገቢ የሚደረግ መሆኑ በፅሑፍ ይገለፅለታል፡፡

4. የሐራጅ አሸናፊ ማስጠንቀቂያው ከደረሰው ቀን ጀምሮ በሰባት ቀን ጊዜ ውስጥ በልዩነት የሚፈለግበትን ሂሣብ ገቢ ካላደረገ ሐራጅ ተሠርዞ ያስያዘው ገንዘብ ለመንግሥት ገቢ ይደረጋል፡፡

5. የሐራጅ አሸናፊ ቀሪውን ሂሣብ ባለመክፈሉ ሐራጁ የተሠረዘ እንደሆነ ሐራጁ የመጀመሪያ ከሆነ የመጀመሪያ ሐራጅ እንዳልተካሄደ ሁለተኛ ሐራጅ ከሆነ ሁለተኛ ሐራጅ እንዳልተካሄደ ይቆጠራል፡፡

31. <u>የተሸጠውን ንብረት ለገዢው ስለማስረከብ፡-</u>

የግብር ባለስልጣኑ/ ከተማ አስተዳደሩ በሐራጅ የተሸጠው ንብረት ዋጋ ሙሉ በሙሉ መከፈሉን ካረጋገጠ፣ ተንቀሣቃሽ ንብረት ከሆነ ለአሸናፊው ወዲያውኑ ያስረክባል፡፡ የማይንቀሣቀስ ንብረትና ለማዛወር ምዝገባ የሚያስፈልገው ንብረት ከሆነ የንብረት ባለቤትነት መብት በገዥው ስም እንዲዛወር አግባብ ላለው የመንግሥት አካል በጽሑፍ ያስታውቃል፡፡ የንብረቱ ባለቤት ወይም ሕጋዊ ወኪሉ ይህንኑ በግልባጭ እንዲያውቀው ያደርጋል፡፡

32. <u>በሐራጅ ያልተሸጠን ንብረት ስለመረከብ፡-</u>

1.በዚህ መመሪያ አንቀጽ 30(1) እንደተመለከተው ሊሸጥ ያልቻለን ንብረት የባለሥልጣኑ መ/ቤት ከተማ አስተዳደሩ እንዲረከበው ውሣኔ የተሰጠ እንደሆነ እና ተቀባይነት ካገኘ ወረዳ ገቢዎች ጽ/ቤት ወይም ከተማ አስተ/ገቢዎች ጽ/ቤት በኩል ይህንኑ ውሣኔ የንብረቱ ባለቤት በጽሑፍ እንዲያውቀው ይደረጋል፡፡

2. የግብር አስገቢው ባለሥልጣን በግምቱ ከተማ አስተዳደሩ የተረከበውን ንብረት ለመንግሥት የተሻለ ጥቅም በሚያስገኝ መንገድ ሊሸጥ ወይም ሊያስተላልፍ ወይም ለባለሥልጣኑ/ ለከተማ አስተዳደሩ ሥራ ሊገለገልበት ይችላል፡፡

33. <u>የግብር ዕዳ ስለማቀናነስ፡-</u>

1. በሐራጅ የተሸጠ ንብረት ወይም ባለሥልጣኑ የተረከበው ንብረት በተሸጠበት ወይም ባለሥልጣኑ በተረከበበት ዋጋ ልክ ከግብር ከፋዩ ከሚፈለግ ዕዳ ላይ እንዲቀነስ ይደረጋል፡፡ የግብር ክፍያ ደረሠኝም ለግብር ባለዕዳው ይሰጣል፡፡

2. በሐራጅ ከተሸጠው ንብረት የተገኘው ገንዘብ በንዑስ አንቀጽ 1 በተመለከተው መሠረት እንዲቀናነስ ከተደረገ በኋላ ግብር ከፋዩ ላይ የሚፈለግ ቀሪ ዕዳ ካለ፣ የባለስልጣኑ መ/ቤት የከተማ አስተዳደሩ ለዕዳው ክፍያ የሚውል የግብር ከፋዩን ሌላ ማናቸውም ንብረት በመያዝ መሸጥ ይቻላል፡፡ ግብር ከፋዩም የሚፈለግበት ግብርና ወጪ ከተቀነሰ በኋላ ተራፊ ሂሣብ ካለው ወዲያውኑ ይመለስለታል፡፡

34. <u>ንብረት የመያዝና የመሸጥ ወጪዎች፡-</u>

የግብር ባለዕዳውን ንብረት በመያዝና በመሸጥ ለግብር ዕዳ መክፈያ የማዋል ሥርዓት ወጪዎች የሚባሉት የሚከተሉት ናቸው፡፡

1. ተሽከርካሪ መጐተቻ ወጪ

2. የተያዙ ዕቃዎችን ለማጓጓዝ የወጣ ወጪ፣

3. የመጋዘን ወጪ፣

4. የቁልፍ መቁረጫና አዲስ ቁልፍ መግዣና ማስገጠሚያ

5. የሐራጅ ማስታወቂያ ልዩ ልዩ ወጪ፣

6. ለአጫራቾች የአገልግሎት ክፍያ፣

7. ዋጋ ማስተመኛ

8. የፖሊስ ድጋፍ ሲጠየቅ ለፖሊስ አባሉ የሚከፈል የአበል ወጪ

9. ሌሎች ልዩ ልዩ ወጪዎች፣ ከሥራው ጋር ተያያዥነት ያላቸው ተገቢ ደረሰኞች ሲቀርቡ፣

35. <u>የሚፀናበት ቀን፡-</u>

ይህ መመሪያ ከ_________2003 ዓ.ም. ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት**

**ገቢዎች ባለሥልጣን**

**<u>ባህርዳር</u>**

**አባሪ 1**

## በአብክመ ገቢዎች ባለሥልጣን

## ንብረት/ሀብት ስለማስከበርና ስለመያዝ የሚሰጥ ማስታወቂያ

ቀን.................................................

ቁጥር...............................................

የተ.እሴት ቁጥር...............................

የግብር ከፋዩ መለያ ቁጥር.................

ለ ___________________________________

አድራሻ፡– ክልል ______________________ ዞን __________________ ወረዳ __________________

ከተማ ____________________ቀበሌ ____________ የቤ.ቁ __________________ ስልክ ቁጥር ______________

| ተ.ቁ | የግብር /ታክስና የኪራይና የአገ/ክፍያ | | የገንዘብ መጠን | | የተከፈለ | | በቀሪ የሚፈለግ ግብር/ታክስ | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ዓይነት | ዘመን | ብር | ሣ | ብር | ሣ | ብር | ሣ |
| | | | | | | | ወለድ<br>መቀጫ | |
| | | | | | | ድምር | | |

ከላይ መጠኑ ለተገለፀውና ለታክሱ ባለስልጣኑ/ለከተማ አስተዳደሩ መከፈል ያለበት ግብር፣ ታክስና የአገ/ክፍያ የሚፈለግብዎ መሆኑን በማመልከት በቀን ---------------- በቁጥር -------------- በተመዘገበ የግብርና ታክስ ውሳኔ ማስታወቂያ እንዲደርስዎ መደረጉ ይታወቃል፡፡

ሆኖም ግን የተጠቀሰውን የግብር /ታክስና የአገ/ክፍያ ዕዳ የያዘ የግብር/ታክስ ውሣኔ ማስታወቂያ የደረስዎ ቢሆንም የግብር/ታክስ ግዴታ ለመወጣት ፈቃደኛ ሣይሆኑ ቆይተዋል፡፡

ስለዚህ ተፈላጊውን የግብር ወይም ታክስ ግዴታወን ፈፅመው ባለመገኘትዎ በግብር ወይም ታክስ በአዋጅ ቁጥር 76/94 አንቀጽ 78 እንዲሁም በከተሞች የፋይናንስ ደንብ ቁ37/1998 አንቀጽ 13.4 መሠረት የግብር፣ ታክስና የአገ/ክፍያ ከፋዩን ማናቸውም ንብረት በመያዝና በመሸጥ ለግብሩ ወይም ለታክሱ ዕዳ እንዲያውል ለታክስ ባለስልጣኑ ለከተማ አስተዳደሩ ስልጣን የተሰጠ በመሆኑ ይህ ማስታወቂያ ከደረሰዎት ጊዜ ጀምሮ ማናቸውም የሚንቀሳቀስና የማይንቀሳቀስ ንብረትዎ ለግብር ታክስና የአገ/ክፍያ አሰባሰብ ዕዳውና ከዚሀ ጋር ለተያያዙ የአፈፃፀም ተግባሮች ማከናወኛ ለሚወጣ ወጭ መሸፈኛ የተከበረ መሆኑን እናስታውቃለን፡፡

የኃላፊ ፊርማ

ግልባጭ፣

-----------------

-----------------

-----------------

## በአብክመ ገቢዎች ባለሥልጣን

### ንብረት /ሀብት/ ስለመያዝ የሚሰጥ ማስታወቂያ

ቀን.................................................

ቁጥር...............................................

ለ _______________________________

_______________________________

በግብር ከፋዩ መለያ ቁጥር.................በተ.እሴት ቁጥር................................ የተመዘገቡትና አድራሻቸው ክልል_________________ ዞን _________________ ወረዳ ______________________
ከተማ _________________ቀበሌ __________ የቤ.ቁ ________________ ስልክ ቁጥር ___________
የሚገኙት ግብር ከፋይ አቶ/ወ/ሮ ___________________ከታች የተመለከተውን ----------------------------- .......................................................................................................... መከፈል ያለበት የግብር/ታክስና የአገ/ክፍያ መሆኑን በማመልከት በቀን ------------ በቁጥር ---------------- የተመዘገበ የግብር ውሳኔ ማስታወቂያ እንዲደርሳቸው የተደረገ ቢሆንም ግዴታን ለመወጣት ፈቃደኛ ባለመሆን የተጠቀሰው የግብር/ታክስና የአገ/ክፍያ ዕዳ ሣይከፈል ይገኛል፡፡

| ተ.ቁ | የግብር /ታክስና የአገ/ክፍያ | | የገንዘብ መጠን | | የተከፈለ | | በቀሪ የሚፈለግ ግብር/ታክስና የአገ/ክፍያ | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ዓይነት | ዘመን | ብር | ሣ | ብር | ሣ | ብር | ሣ |
| | | | | | | | ወለድ<br>መቀጫ | |
| | | | | | | ድምር | | |

በፊደል ______________________________________________________

በመሆኑም ይህ ማስታወቂያ በደረሰዎት ጊዜ በግብር/ታክስ ከፋዩ ስም የተቀመጠለት ገንዘብ ወይም ሊከፍሉት የሚገባ ማናቸውም አይነት ክፍያ ወይም በእጅዎ/በይዛታዎ/ የሚገኘው የግብር/ታክስ ከፋዩ ንብረት ወይም በንብረቱ ላይ ያለው መብት በአዋጅ ቁጥር 76/94 አንቀጽ 78 እንዲሁም በከተሞች የፋይናንስ ደንብ ቁ 37/1998 መሠረት በገቢዎች ባለሥልጣን ስም እንዲከበር ተወስኗል፡፡

ስለዚህ በማስታወቂያው መሠረት ባላስልጣኑ መ/ቤት በከተማ አስተዳደሩ ስም የተከበረው ሃብት/ንብረት በአዋጅ ቁጥር 76/94 አንቀጽ 78 መሠረት » በግብር/ታክስ ከፋዩ ስም የተቀመጠለት ገንዘብ ወይም ሊከፍሉት የሚገባ ማናቸውም ዓይነት ክፍያ ለታክስ ባለሥልጣኑ ከተማ አስተዳደሩ በ ________ የሥራ ቀናት ጊዜ ውስጥ ገቢ እንዲያደርጉ ወይም በእጅዎ/በይዞታዎ የሚገኝ የግብር/ታክስ ከፋዩ ማናቸውም ንብረት ለግብር/ታክስ ዕዳ አሰባሰብ እንዲውል ለታክስ ባለሥልጣኑ የከተማ አስተዳደሩ በ ____________ የሥራ ቀናት ጊዜ ውስጥ እንዲያስረክቡ የተወሰነ መሆኑን እናስታውቃለን፡፡

የኃላፊ ፊርማ

ግልባጭ፣

_______________

_______________

_______________

አባሪ 3

## የሐራጅ ሽያጭ ማስታወቂያ

ግብር ከፋዩ ---------------------------------------------- የሚፈለግባቸውን ግብር/ታክስና የከተማ አገልግሎት ክፍያ ብር ስላልከፈሉ አድራሻው ክልል ------------------------- ዞን ----------------------- ወረዳ/ከተማ ----------------- ቀበሌ --------------------- የቤት ቁጥር ------------------------- የሆነውን የግብር ባለዕዳውን ንብረቶች በአብክመ ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ግብር አዋጅ ቁጥር 76/94ና በከተሞች ፋይናንስ ደንብ ቁ37/1998 በተሰጠው ሥልጣን መሠረት የሚሸጠው ንብረት_ዓይነት ------ ---------------------------------------------------------------------------------------------------- ባለበት ሁኔታ በሐራጅ ለመሸጥ ይፈለጋል፡፡

1. የንብረቱ የሐራጅ መነሻ ዋጋ ግምት ብር ---------------- ነው ፡፡
2. የተጫራቾች የምዝገባ ሰዓት ከ--------------------- እስከ ----------------- ሰዓት ሆኖ የሐራጁ መዝጊያ ሰዓት --------------- ይሆናል፡፡
3. ተጫራቾች በቅድሚያ የሐራጁን መነሻ ዋጋ 1/4ኛውን በጥሬ ገንዘብ ወይም በባንክ የክፍያ ማዛዣ ሲ.ፒ.ኦ ማስያዝ አለባቸው
4. ለተሸናፊ ተጫራቾች ያስያዙት ገንዘብ ወዲያውኑ ይመለስላቸዋል፡፡
5. አሸናፊው ያስያዘው ገንዘብ ከግዥው ዋጋ ጋር ይታሰብለታል፡፡ ጠቅላላ ዋጋው ቀሪውን የሐራጅ ጨረታው ከተካሄደበት ቀን ጀምሮ ባሉት 15 ቀናት ውስጥ አጠናቆ በመክፈል ንብረቱን መረከብ አለበት፡፡
6. የጨረታው አሸናፊ ያሸነፈበትን ጠቅላላ ዋጋ በ15 ቀናት ውስጥ አጠናቆ የማይከፍል ቢሆን ለጨረታው በዋስትና ያስያዘው ገንዘብ ለመ/ቤቱ ገቢ ሆኖ የጨረታው አሸናፊነቱ ይሠረዛል፡፡
7. ንብረቱ በጨረታ እንዳይሸጥ የሚቃወም ቢኖር ከፍ/ቤት የእግድ ትዕዛዝ ማምጣት አለበት፡፡
8. ስለ ንብረቱ አሻሻጥ ዝርዝር መረጃ ከ---------------- ክፍል ማግኘት ይቻላል፣
9. ባለሥልጣኑ ከተማ አስተዳደሩ ስለንብረቶቹ አሻሻጥ የተሻለ መንገድ ካገኘ ጨረታውን በሙሉም ሆነ በከፊል ሊሠርዝ ይችላል፣

# የጨረታ ሽያጭ ማስታወቂያ

ግብር ከፋዩ ---------------------------------------- የሚፈለግባቸውን ግብርና ታክስ እንዲሁም ኪራይና የአገ/ክፍያ ስላልከፈሉ አድራሻው ወረዳ/አስተዳደር ------------------- ቀበሌ የቤት ቁጥር --------------- የሆነው የግብር ባለዕዳውን ንብረቶች የግብር አስገቢው ባለሥልጣን ከተማ አስተዳደሩ በ--------------- አዋጅ/ደንብ ቁጥር -------------------- በተሰጠው ሥልጣን መሠረት የሚሸጠው ንብረት ዓይነት --------------------------------------------------------------------- በጨረታ ለመሸጥ ይፈልጋል።

1. የንብረቱ የጨረታ መነሻ ዋጋ ግምት ብር ---------------- ነው።
2. ስለንብረቱ አሻሻጥ መረጃ ከ------------------- ክፍል ማግኘት ይቻላል።
3. ተጫራቾች በቅድሚያ የጨረታ መነሻ ዋጋ 1/4ኛውን በጥሬ ገንዘብ ወይም ሲ.ፒ.ኦ ማስያዝ አለባቸው።
4. ተጫራቾች ንብረቱን የሚገዙበትን ዋጋ በግልጽ በማስፈር በስም በታሸገ ኤንቬሎኘ አድርገው አድራሻው እንደአግባብነቱ ለከተማ አስ/የገቢዎች /ጽ/ቤት ወይም ለወረዳ ገቢዎች ጽ/ቤት በማለት አስፍረው እስከ ------------- ቀን ------------- ዓ.ም. ከቀኑ -------------- ሰዓት ድረስ ቢሮ ቁጥር ----------- በተዘጋጀው ሳጥን ማስገባት አለባቸው።
5. ጨረታው ------------------ ቀን ------------ ዓ.ም. በቀኑ ------------- ሰዓት ተዘግቶ በ------------------- ቀን በ---------------- ሰዓት ተጫራቾች ወይም ሕጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት በ----------------- አዳራሽ/ቢሮ ይከፈታል።
6. አሸናፊው ያስያዘው ገንዘብ ከገዥው ዋጋ ጋር ታስቦ ያሸነፈበትን ጠቅላላ ዋጋ አሸናፊነቱ ከተገለፀበት ቀን ጀምሮ ባሉት 15 ቀናት ውስጥ አጠናቆ በመክፈል ንብረቱን መረከብ አለበት።
7. የጨረታው አሸናፊ ያሸነፈበትን ጠቅላላ ዋጋ በ15 ቀናት ውስጥ አጠናቆ የማይከፍል ሲሆን ለጨረታው በዋስትና ያስያዘው ገንዘብ ለመ/ቤቱ ገቢ ሆኖ የጨረታው አሸናፊነቱ ይሰረዛል።
8. ጽ/ቤቱ ስለንብረቶቹ አሻሻጥ የተሻለ መንገድ ካገኘ ጨረታውን በሙሉም ሆነ በከፊል ሊሰርዝ ይችላል።

# <u>በአብክመ ገቢዎች ባለሥልጣን</u>

# <u>በግብር/ታክስና የአገ/ክፍያ ዕዳ ምክንያት የተያዘ ንብረት</u>

# <u>የጨረታ ሽያጭ አፈጻጸም ሪፖርት</u>

ቀን --------------------- ዓ.ም.

1. ጨረታ የተካሄደበት ቀን ------------------------

   "     "     ቦታ -------------------------

   "     "     ሰዓት ------------------------

2. የጨረታ አስፈጻሚዎች/የገቢ አሰባሰብ ክትትል ባለሙያዎች/

| *ስም* | *ፊርማ* |
|---|---|
| 1. ------------------------------ | ------------------------ |
| 2. ------------------------------ | ------------------------- |
| 3. ------------------------------ | ------------------------- |

3. የግብር/ታክስ ባለዕዳ ስም ለሚፈለግበት የግብር/ታክስ ዕዳ አሰባሰብ በ------------- በወጣው የጨረታ ሽያጭ ማስታወቂያ ዝርዝራቸው ቀጥሎ የተመለከቱት/አባሪ የተደረገው የንብረት ዓይነቶች
4. በጨረታው ለመካፈል የቀረቡ ተጫራቾች ዝርዝር ይገለጽ ------------------- በጥሬ ገንዘብ/በያዥ በማስያዝ ተመዝግበው ተጫርተዋል፡፡
5. የጨረታው አካሄድ በአጭሩ ይገለጽ

   ------------------------------------------------------------------------------------------------

   ------------------------------------------------------------------------------------------------

6. የገቢ አሰባሰብ ክትትል ባለሙያዎች አስተያየት

   ------------------------------------------------------------------------------------------------

   ------------------------------------------------------------------------------------------------

7. የጽ/ቤቱ ዋና ኃላፊ ውሳኔ

   ------------------------------------------------------------------------------------------------

   -----------------------------------------------------------------------------------------------.

ሙሉ ስም -----------------------------

ኃላፊነት ------------------------------

ፊርማ -----------------------------